የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር
የ2014 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

ነሐሴ/ 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር
የ2014 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የተመደበለትን የመደበኛና ካፒታል በጀት በፋይናንስ አዋጅ፣ ደንብ እና በተከታታይ በወጡ መመሪያዎች መሠረት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ ከዚህ ሪፖርት ጋር የተያያዙትን የ2014 በጀት ዓመት የሂሳብ ሪፖርቶች እና ማስታወሻዎች ኦዲት አድርገናል።

የሂሳብ ሪፖርቶቹን የማዘጋጀት የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶቹን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው ።

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ዓለምአቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን መሠረት በማድረግና የዋና ኦዲተርን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው። እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ (የኦዲት አስተያየት) ለመስጠት ያስችለናል።

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በሚንስቴር መ/ቤቱ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው ።

ኦዲቱ የተከናወነው በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር በመከላከያ ሰራዊት አዋጅ ቁጥር 1100/2011 አንቀጽ 71 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት በማድረግ በሚስጥር የሚያዙና የሚጠበቁ መረጃዎች ፣ ሰነዶችና ንብረቶች እንዲሁም ይህንን አስመልክቶ በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት በቁጥር መ40-712/1 በቀን 17/12/2011 ዓ/ም በተጻፈው ደብዳቤ መሠረት ለኦዲት በቀረቡት ሂሳቦች የዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተለው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርት ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዞ ቀርቧል::

- የተጠቃለለ የሙከራ ሂሣብ ሚዛን ሪፖርት

የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት በትክክል የተዘጋጁ

እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

ወጪ፤

1. በፌዴራል መንግሥት የክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ዳይሬክቶሬቱ ወጪዎችን የሚመዘግበው በፋይናንስ መመሪያው መሠረት ዕቃው ወይም አገልግሎቱ ሲቀርብ ሲሆን ዕቃው ወይም አገልግሎቱ እስኪቀርብ ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ መያዝ እንዳለባቸው ተመልክቷል። ይሁን እንጂ በመመሪያው መሰረት የሚፈፀም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

የመከላከያ ጠቅላይ መምሪያ ጠቅላላ አገልግሎት ዋና ዳይሬክቶሬት፤

ዳይሬክቶሬቱ ሰኔ 29 ቀን 2014 ዓ.ም በወጪ ቫውቸር ቁጥር 80311 ለመከላከያ ጠቅላይ መምሪያ ጠቅላላ አገልግሎት ዋና ዳይሬክቶሬት የሦስተኛ ምዕራፍ የገፀ ምድር ማሰዋብ እና የሕንፃ ግንባታ ሥራ ማስጀመሪያ ለኤቶል ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ ብር **654,133,864.31** የቅድሚያ ክፍያ የፈጸመ ሲሆን፤ መ/ቤቱ አገልግሎቱን ሳያገኝ ክፍያው በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል።

2. የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ተ.ቁ 2/ለ ወጪ ከመደረጉ በፊት ስለወጪው የተሟላ ማስረጃ መቅረቡና ስልጣን ባለው አካል መፈቀድ እንዳለበት ይገልጻል። በመሆኑም በዚህ መመሪያ መሰረት መከናወኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

በማዕከል ሂሳብ ምዝገባ፤

በውጭ ሀገር ተመድበው በመስራት ላይ ለሚገኙ ወታራዊ አታሸዎች የህይወት መድህን ዋስትና በሚል በቀን 30/10/2014 በሂሳብ መደብ 6254 ብር **15,302,696.53** የተከፈለ እንዲሁም በተለያዩ የውጪ አገራት ለሚገኙ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ መከላከያ ሠራዊት ተማሪዎች አገልግሎት የሚውል የኪስ ገንዘብ፣ ለምግብ፣ ለቤት ኪራይ፣ ለጥናትና ምርምር እና ለትምህርት ክፍያ በሚል ወጪ የሆነ ብር **26,417,441.4፤** ለክፍያው ተገቢው ማስረጃ ከሚመለከተው አካል ሳይቀርብ በድምሩ ብር **41,720,137.93** በወጪ ተይዞ ተገኝቷል፡፡

3. የመከላከያ ሠራዊት አዋጅ ቁጥር 1100/2012 ክፍል ሰባት አንቀፅ 71 ንዑስ አንቀፅ 3 መሠረት ሚ/መ/ቤቱ በሒሣብ መዛግብቶች ላይ ለውጭ ኦዲተሮች የማይቀርቡ ብሎ የማዕከል ሂሳብ ምዝገባ በዝርዝር ባቀረባቸው የሒሣብ መደቦች ውስጥ ለወታደራዊ አገልግሎት የሚውሉ እና ለሠራዊቱ ሰብዓዊ አገልግሎት የሚውሉ የሒሣብ መደቦች ተለይተው የቀረቡ ቢሆንም፤

በማዕከል ሒሳብ ምዝገባ፤

የሒሣብ መደብ 6313 ሚስጢራዊ የወጪ ሂሳብ አርዕስት ተብለው ከተለዩት የሂሳብ መደቦች ጋር እንዲካተት በመደረጉ እና በዚሁ የሂሳብ መደብ በወጪ ለተያዘው ብር 50,393,848.97 የወጪ ማስረጃ ባለመቅረቡ የወጪውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ተከፋይ ሂሳብ፤

4. በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት የገቢ፣ የወጪ፣ የተሰብሳቢ፣ የተከፋይና የመሳሰሉት ሒሳቦች የዴቢት ወይም የክሬዲት መደበኛ ሚዛናቸውን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

በማዕከል ሒሳብ ምዝገባ፤

በ2014 በጀት ዓመት የሰኔ ወር የማዕከል ሒሳብ ምዝገባ በባንክ አካውንት ቁጥር 01 (1000000984721) የተጠቃለለ የሒሳብ ሪፖርት መዝጊያ ላይ በሂሳብ መደብ 5004 የሚታይ ብር 43,205,401.45. እንዲሁም በ5054 ብር 19,786,665.11 ተከፋይ ሂሳቦች በድምሩ ብር 62,962,066.56 በዴቢት ሚዛን የሚታዩ መሆኑ ታውቋል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 በተገለጹት ሁኔታዎች መሠረታዊነትና ጉልህነት የተነሳ እንዲሁም ከታች በተራ ቁጥር 14 ላይ በተገለጸው ምክንያት የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርቶች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ የተሰበሰበውን ገቢ የተከፈለውን ወጪና የበጀት አጠቃቀም በትክክል ያሳያሉ ብሎ አስተያየት መስጠት አልተቻለም፡፡

ህጋዊነትን ያልተከተሉ ጉዳዮች (Compliance Matters)፤

ገቢ፤

5. ህዳር 1999 የወጣው የፌዴራል ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች የውጭ አገር ነፃ ህክምና መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 5.1 መሰረት የአገር ውስጥና የወጭ አገር ህክምና እንዲያገኙ የተፈቀደላቸው የመንግስት ሀላፊዎች ከደመወዛቸው 2% እንዲሁም የሀገር ውስጥ ህክምና ብቻ እንዲያገኙ የተፈቀደላቸው ኃላፊዎች በየወሩ ከደመወዛቸው 1% መዋጮ መክፈል አለባቸው ይላል ፡፡ ይሁን እንጂ፤

በመከላከያ ኢንተርፕራይዝ ዘርፍ

ከዘርፉ ኃላፊዎች ደመወዝ ተቀናሽ መደረግ የሚገባው የህክምና መዋጮ በመመሪያው መሰረት ባለመቀነሱ በድምሩ ብር 7,210.72 ገቢ አለመደረጉ ታውቋል፡፡

ወጪ፤

6. የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ዓ.ም በክፍል ሁለት ስለመንግስት ገንዘብ ክፍያ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት ክፍያ ለሚፈፀምባቸው ወጪዎች ተገቢው የሰነድ ማስረጃ መቅረብ እንደሚገባው ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ፤

በአየር ኃይል ጠ/መምሪያ

በደረጃ 3 ሆስፒታል የሲቪል የህክምና ሙያተኞች የትርፍ ሰዓት/ዲዩቲ ክፍያ፤ የክፍያ ማረጋገጫና መከታተያ ቅፅ፤ የሐኪሞቹ የሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓትን የሚገልፅ ዝርዝር መረጃ (On and Off) ሳይቀርብ በሂሳብ መደብ 6121 ለሕክምና ባለሙያዎች በድምሩ ብር **554,300.82** የትርፍ ሰዓት ክፍያ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

7. የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ወይም የቀድሞው የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ታህሳስ 16 ቀን 2005 ዓ.ም በቁጥር ሰሰሚ30/ጠ/18/22/459 በተጻፈ ደብዳቤ ስለኮንትራት/ጊዚያዊ ቅጥር ባስተላለፈው መመሪያ መሰረት ማንኛውም የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት እጅግ አስፈላጊ ለሆነ እና ለአጭር ጊዜ ብቻ የኮንትራት/ጊዚያዊ ቅጥር መፈጸም አስገዳጅ ሁኔታ ከተፈጠረ ጥያቄው በቅድሚያ ለሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር እየቀረበ ተቀባይነት ማግኘቱ መረጋገጥ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ ይሁን እንጂ፤

በመከላከያ ኢንተርፕራይዝ ዘርፍ

የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴርን ሳያስፈቅድ ከሀምሌ1/2013 እስከ ሰኔ 30/2014 ዓ.ም 14 ሠራተኞችን በኮንትራት ቀጥሮ ብር **530,808.00** ክፍያ ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

8. የኢ.ፌዲሪ መከላከያ ሠራዊት መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 460/2012 ክፍል 4 አንቀጽ 33 መሠረት መከላከያ ሚኒስቴር የትምርት ዕድል ለሰጣቸው ሰራተኞች ውል የሚያስገባ እና በተጨማሪም የትምህርት ዕድል ያገኙት ተማሪዎች ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ በገቡት የውል ግዴታ መሰረት ግዴታቸውን የተወጡ መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፤

በማዕከል ሂሳብ ምዝገባ፤

በሚ/መ/ቤቱ ትምህርት ዕድል አግኝተው በተለያዩ የውጭ ሀገራት ትምህርታቸውን እየተከታተሉ የሚገኙ በርካታ ተማሪዎች ውል ሳይገቡ በድምሩ ብር **26,352,903.49** የትምህርት ክፍያ ተፈፅሞ መገኘቱ ታውቋል፡፡

9. የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ተ.ቁ 2/ለ ወጪ ከመደረጉ በፊት ስለወጪው የተሟላ ማስረጃ መቅረቡና ስልጣን ባለው አካል

መፈቀድ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በመሆኑም በዚህ መመሪያ መሰረት መከናወኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

<u>በማዕከል ሂሳብ ምዝገባ፤</u>

76 የኢፌዲሪ መከላከያ አባላት በራሽያ አገር በተለያዩ ኮርሶች ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ የሚገኙ ሲሆን ለተማሪዎች ለኪስ፣ ለምግብ፣ለቤት ኪራይ፣ ለትራንስፖርት፣ ለቪዛ እና ለባንክ ክፍያ የሚሆን በቀን 8/01/2014 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 214012 በሂሳብ መደብ 6272 ብር 9,340,980.68 ወጪ በማድረግ ክፍያ የተፈፀመ ቢሆንም የኢፌዲሪ ኢምባሲ የመከላከያ አታሼ ጽ/ቤት ሞስኮ በደብዳቤ ቁጥር ሞስኮ/መሐ/+/24/14 በቀን 06/03/2014 የተላከላቸው ገንዘብ በአካውንት ቁጥር መቀየር ምክንያት እንዳልደረሳቸው አሳውቀዋል፡፡ በዚህም መሠረት የፋይናንስ ማዕከሉ የተመለሰውን ገንዘብ ምዝገባ ሲያከናውን በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 475818 ሂሳብ መደብ 4103 ብር 8,916,564.67 ዴቢት በ6272 ብር **8,916,561.67** ክሬዲት በማድረግ ምዝገባ ሲከናወን ብር **424,416.01** ወጪ ለመደረጉ ማስረጃ ያልቀረበለት መሆኑ ታውቋል፡፡

10. በፌደራል መንግስት የፋይናስ አስተዳደር የወጣ የሚነስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 ክፍል አምስት አንቀፅ 16 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ላይ የመንግስት ገንዘብ ክፍያ የሚፈፀመው ወይም ወጪ የሚደረገው ገንዘብ ክፍያው ወደሚፈፀምለት ባለመብት የባንክ ሂሳብ በማስተላለፍ ይሆናል፡፡ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ቢኖርም ወጪ በቼክ፣ በሌተር ኦፍ ክሬዲት፣ ወይም በጥሬ ገንዘብ፣ የሚፈፀምበት ሁኔታ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡ እንዲሁም የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት ስለመንግስት ገንዘብ ክፍያ የመደበኛ ስራ ማስኬጃ ወጪዎች ሲፈፀሙ መሟላት አለባቸው ብሎ ከዘረዘራቸው ውስጥ በተ/ቁጥር 4 ላይ ክፍያ ለሚፈፀምባቸው ወጪዎች ተገቢው የሰነድ ማስረጃ መሟላት እንዳለባቸው እና በማስረጃነት መቅረብ ያለበት ኦሪጅናል ደረሰኝ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ፤

<u>በማዕከል ሂሳብ ምዝገባ፤</u>

መስሪያ ቤቱ በ2014 ዓ.ም ከናሽናል ኦይል ኢትዮጵያ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ቅባትና ነዳጅ ለማዕከሉና ለተለያዩ ቅርንጫፎች ለማቅረብ ውል በመግባት ግዥ ለተፈፀመበት በድምሩ ብር **732,195,637.69** ወጪ የተደረገ ሲሆን፤ ወጪው በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ ተወራርዶ መገኘቱ ታውቋል፡፡

11. የፌደራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 ክፍል 7 አንቀጽ 28.5 ንዑስ አንቀጽ (መ) መሠረት የመከላከያ ኢንተርፕራይዝ ዘርፍ የግንባታ ሥራዎቹን በአማካሪ መሐንዲስ እያሰራ ክፍያ መከፈል እንደሚገባ ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ፤

በመከላከያ ኢንተርፕራይዝ ዘርፍ፤

ለወንጪ ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ግንባታ ከመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ ጋር በአንድ አመት ማለትም በ365 የስራ ቀናት የሚጠናቀቅ የብር 35,620,287.62 የግንባታ ስምምነት ውል ፈጽሟል፡፡ ይሁን እንጂ ሥራ ተቋራጩ በ22/09/2021 (12/1/2014) ውል ገብቶ የመጀመሪያ ቅድሚያ ክፍያ (30 በመቶ) በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 878448 ብር 10,686,086.29 የተከፈለ ሲሆን፤ ውል ከተፈፀመበት ቀን እስከ ሰኔ 30/2014 ዓ.ም ድረስ የግንባታ ስራውን ሳይከታተል እና ምንም አይነት ቁጥጥር ሳያደርግ ከታህሳስ/ 2014 ጀምሮ በወር ብር 101,196.43 (101,196.43*7) በድምሩ ብር **809,571.44** ለግንባታ ስራው አማካሪ የመከላከያ ኮንስትራክሽን ዲዛይን ድርጅት ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

12. የፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ጥራዝ 2 የሂሳብ አወቃቀር ሥርዓት ወጪዎች በትክክለኛ የሂሳብ መደባቸውን ጠብቀው ተመዝግበው ሪፖርት መደረግ እንዳለባቸው በሚያዘው መሠረት ለመከናወኑ ኦዲት ሲደረግ፡

በአየር ኃይል ጠ/መምሪያ

ለተለያዩ ዕቃዎች መግዣ እና ለአበል የተከፈለ በድምሩ ብር **2,965,353.64** በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

13. የፌደራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀፅ 9 ላይ ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎች ማንኛውም ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ንዑስ አንቀፅ 3 ላይ ዕቃው ወደ መሥሪያ ቤቱ ዕቃ መጋዘን ለመግባቱ የዕቃ ገቢ ደረሰኝ /ሞዴል19/ መቅረቡ ተረጋግጦ ክፍያው መፈፀም እንዳለበት ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ

በአየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ

የተለያዩ ዕቃዎች ለተገዙበት የተከፈለ ብር **32,974.74** በወጪ የተያዘ ሲሆን ንብረቱ ገቢ ለመደረጉ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለት መሆኑ ታውቋል፡፡

14. <u>በበጀት ዓመቱ ኦዲት ያልተሸፈኑ ወጪዎች፤</u>

የሀገር መከላከያ ሚ/ር ጥር 2011 ዓ/ም በአዋጅ ቁጥር 1100/2011 አንቀጽ 71(3)ን መሠረት አድርጎ በሚኒስትሩ በወጣው መመሪያ ቁጥር መ40-712/1 መሠረት ሚስጢር በመሆናቸው ኦዲት የማይደረጉ የወጪ ሂሳቦች ተብለው ዝርዝር በመቅረቡ ምክንያት በ2014 በጀት ዓመት ከተመዘገበው ከመ/ቤቱ ጠቅላላ ወጪ ብር **91,603,663,965.01** ውስጥ ብር **72,914,645,634.55** (79.5%) በመ/ቤታችን ኦዲት አልተደረገም ፡፡

ተሰብሳቢ ሂሳብ፤

15. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ፤ በመመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ደግሞ ለሥራ ማስኬጃ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል። ይሁን እንጂ፣ **በማዕከል ምዝገባ፤** ብር **22,711,253,888.30 ፤ በአየር ኃይል ጠ/መምሪያ** ብር 19,486,751.01 **በመከላከያ ኢንተርፕራይዝ ዘርፍ** ብር 2,729,396.40; እንዲሁም **በመከላከያ ጠቅላይ መምሪያ ጠቅላላ አገልግሎት ዋና ዳይሬክቶሬት** ብር 4,490,023.81፤

በድምሩ ብር 22,737,960,059.52 በደንቡ መሰረት በወቅቱ ሳይወራረድ በተሰብሳቢ ተይዞ ተገኝቷል፡፡

ተከፋይ ሂሳብ፤

16.በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚገኙት ተከፋይ ሂሳቦች በተጨማሪ ዕሴት ታክስ እንዲሁም በቅድሚያ ግብር አዋጅ ደንብና መመሪያ መሰረት እንዲሁም ከሚኒስቴሩ ጋር በተገባው ውል መሰረት በወቅቱ የሚከፈሉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ:-

በማዕከል ሒሳብ ምዝገባ ብር 5,327,063,328.92 እንዲሁም **በአየር ኃይል ጠ/መምሪያ** ብር 607,836.32፤ በድምሩ ብር 5,327,671,165.24 ለባለመብቱ ሳይከፈል በተከፋይ ተይዞ ተገኝቷል።

በጀት፤

17. የፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል ሶስት አንቀጽ 12(1) ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ለበጀት አመቱ የተፈቀደለትን የመደበኛም ሆነ የካፒታል በጀት አጠቃቀም በሚገባ መቆጣጠር እንዳለበት ይገልጻል:: ይሁን እንጂ፣

- **በማዕከል ሒሳብ ምዝገባ** ብር 1,338,155,955.60፣ እንዲሁም **በአየር ኃይል ጠ/መምሪያ** ብር 22,441,139.77 በድምሩ ብር 1,360,597,095.37 ያልተሰራበት በጀት ተገኝቷል ።

ሌሎች ጉዳዮች፤

ንብረት፤

በአየር ኃይል ጠ/መምሪያ ግቢ፤

- በ2014 ዓ/ም የቋሚ ዕቃዎች ዓመታዊ ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑ፤
- በቋሚ ንብረቶች ላይ የንብረት መለያ ኮድ(ቁጥር) ያልተለጠፈ ወይም ያልተጻፈባቸው መሆኑ፣
- ብዛት ያላቸው አሉሚኒየም፤ በርካታ አሮጌ ተሽከርካሪዎች፣ የመኪና እና የአውሮፕላን ጎማዎች፤ ቁርጥራጭ ብረቶች ለፀሐይና ለዝናብ ተጋልጠው በሜዳ ላይ ተከማችተው ተገኝተዋል፡፡

የመከላከያ ጠቅላይ መምሪያ ጠቅላላ አገልግሎት

- የሲቪል ኮንትራት ሠራተኞች የደንብ ልብስ ብትን ጨረቅ ቢን ካርድ ሳይዘጋጅለት በዕቃ ግምጃ ቤት መገኘቱን፤
- ለቋሚ ዕቃዎች የትውስት ፎርም (user card) ሳይዘጋጅ በሞ/22 ወጪ እየተደረገ ለተጠቃሚዎች የሚሰጥ መሆኑ፤
- በዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ ጉዳያቸው በሕግ የተያዙ የተለዩ ንብረቶች ውሳኔ ሳያገኙ በዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ መገኘታቸው ለምሳሌ (ስምንት ዴል ኮምፒውተር፣አንድ የሙዚቃ መሣሪያ(ከበሮ))፤
- የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ንብረት በአንድ ግምጃ ቤት ውስጥ የሚቀመጡ እና ከፍተኛ የመጋዘን የንብረት ክፍል ጥበት መኖሩ፤
- አንድ የከለር ፕሪንተር ቀለም 5270 በሞ/22 ቁጥር 098303 ብዛቱ 120 ወጪ ሆኖ በስቶክ ካርድ ያልተመዘገበ መሆኑ፤
- በመከላከያ የቤቶች ግንባታ ቢሮ ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ አገልግሎት የማይሰጡ በርካታ የተለያዩ ዕቃዎች ለምሳሌ አሮጌ የድሮ ፕሪነተሮች፤ ዴስክ ቶፕ ኮምፒተሮች፤ በርካታ የተሰባበሩ ኤልሴፕ ጠረጴዛዎች፤ አሮጌ ቴሌቪዥኖች፤በርካታ ተሽከርካሪ ወንበሮች፤ UPS ብዛት 90፤ኦሊምፒያ ካልኩሌተር ብዛት 30 ሳይወገዱ መገኘታቸውን፤

በሜጀር ጄኔራል ሙልጌታ ቡሊ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ

- በኮሌጁ ውስጥ የሚገኘው ደረጃ አንድ ሆስፒታል ከመድኃኒት ዋና ግ/ቤት የሚወጡ መድኃኒቶች እና እንዲሁም ለሥርጭት የሚወጣውን መድኃኒት የመጠበቅና ምዝገባ ማካሄድ በአንድ ሰው ብቻ የሚከናወን መሆኑ፤
- ከመድኃኒት ግ/ቤት ለታካሚው የሚወጣውን መድኃኒት የገቢና ወጪ ሥርጭት መቆጣጠሪያ ሥርዓት ያልተዘጋጀ መሆኑ፤
- የመድኃኒት ግ/ቤት የ2014 በጀት ዓመት የንብረት ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑን፤

በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

ከሰላምታ ጋር

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት